## ለ ሚኒሶታ ኢትዮጵያውያን /የኢትዮጵያ ተወላጆች በሙሉ

### ከ ሚኒሶታ ፍትሐዊ ምርጫ ፈላጊ ግብረ ኃይል

(*ይህ ግብረ ኃይል ማንንም ፖለቲካ፣ ሃይማኖት፣ ጾታ፣ እምነትና ዘር የማይወክል ነገር ግን የማህበሩ አባል የሆኑ ምርጫው ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲፈጸም የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ስብስብ መሆኑን እንገልጻለን።፡*)

***በሚኒሶታ የኢትዮጵያ ውያን ማኅበረሰብ የ ሥራ አመራር ምርጫን በተመለከተ***

ይህ መግለጫ በ ዘ-ሐበሻ ጋዜጣ ቅጽ VI ቁጥር 72 በመጋቢት 2007 ዓ.ም እትም ላይ “ ከአስተያየት ሰጪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው” ተብለው ለማኅበረሰቡ (Ethiopian Community) ም/ል ፕሬዝዳንት አቶ መስፍን ነጋያ ስለሚቀጥለው የአመራር መሪዎች ምርጫ የቀረቡትን ጥያቄዎችና አቶ መስፍን ነጊያ የሰጡትን መልሶች ይመለከታል። የማኅበረሰቡ የሥራ አመራር መሪዎች ምርጫ በግንቦት ወር 2007 ዓም (May 2015) እንደሚካሄድ ገልጸዋል። በጣም እናመሰግናለን። ማህበራችንን ማጠናከር የአመራር አባላቶችንም መምረጥ በሚኒሶታ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን መብትና ግዴታ ነው። ማኅበረሰቡ የሁላችንም ቤትና መሰበሰቢያ ነው። ግልጽነትና ተጠያቂነት፣ ኃላፊነትና ግዴታ በሁሉም የሕዝብ አገልግሎት ዘርፎች እጅግ በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። በየትም ቦታ መለመድ ያለባቸው ናቸው። ከዚህ አንጻር የዘ-ሐበሻ ጋዜጣም ሆነ አቶ መስፍን ነጊያ ግልጽ ያላደረጓቸው ጉዳዮች፣ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ያስከተሉ ስለሆነ ምርጫውም በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረዉ በሚችል ሁኔታ እንዲካሄድ የሚከተሉት ዐበይት ጉዳዮች ከምርጫው ቀን በፊት እንዲያርሙ እናሳስባለን፡፡

ሀ) በግንቦት ወር ስብሰባው የሚካሄድበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ዘ-ሐበሻ ጋዜጣ አቶ መስፍን ነጊያን ቢጠይቅ ኖር መልካም ነበር፤ ግን አልሆነም። አቶ መስፍንም የስብሰባውን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ እስካሁን ስላልገለጹ እንዲገልጹ እናሳስባለን፡፡

ለ) በ ዘሐበሻ ጋዜጣ ላይ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ወይም አስመራጭ ኮሚቴንና የምርጫ አፈጻጸምን በሚመለከት አቶ መስፍን ነጊያ ምንም ትንፍንሽ አላሉም፡፡ ሰዓትና ቦታን ለምን መደበቅ አስፈለገ? በመጋቢት (March 21, 2015) በተደመጠው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ሬዲዮ ደግሞ የአመራር ምርጫ ስብሰባ ግንቦት (May, 16, 2015) እንደሚካሄድ እና የሥራ ዘመኑን የጨረሰውን የማኅበረሰቡን የሥራ አመራር ለመተካት በምርጫው መሳተፍ የሚፈልጉ ግለሰቦች እስከ ሚያዝያ ( April 18, 2015) ድረስ የውድድር ማመልከቻ በስልክ እንዲያቀርቡ በ KFAI የኢትዮጵያ ሬዲዮ አስነግሯል። በማህበሩ ውስጠ ደንብ ላይ ፕሬዝዳንቱ 3 ወይም ከሶስት በላይ አባላት ያሉበት የምርጫ ተቆጣጠሪዎች ኮሚቴ ይመድባል፤ የምርጫውንም ውጤት እነዚሁ ግለሰቦች ለፕሬዝዳንቱ ሪፖርት ያደርጋሉ ይላል። ይህን የሚገልጸውን ክፍል ከማህበሩ ድረገጽ ካለው ውስጠ ድንብ ገጽ 4 አንቀጽ 4 እንዳለ እናቀርባለን “***For all votes requiring a ballot, the President or Chairman of the Board shall, prior to the commencement of balloting, appoint a committee of three or more persons of suitable age and experience who shall act as “ Inspectors of Election” and who shall , at the conclusion of such balloting , certify in writing to the President or Chairman the results and the certified copy shall be physically affixed in the minute book to the minutes of that meeting. No inspector of election shall be a candidate for office or shall be personally interested in the question voted upon***” ከዚህ ውጪ በውስጠ ደንቡ ላይ ምርጫንና የምርጫ አፈጻጸምን በሚመለከት የሚገልጸው ቦታ የለም። ከላይ በእንግሊኛ ከተጠቀሰውም ማየት የሚቻለው የምርጫውን ውጤት የምርጫ ተቆጣጣሪዎች ሪፖርት የሚያዳርጉት ለፕሬዝዳንቱ ነው። በራዲዩ ላይ በማህበሩ የተገለጸው ለምርጫ የሚወዳደሩ ግለሰቦች እስከ ሚያዚያ 18 ቀን ስልክ በመደወል እንዲመዘገቡ ጠይቀዋል።ይህን እንዲያዳርጉ የሚፈቅድ ቦታ በውስጠ ደንቡ የለም። ይህ በህግ የሚያስጠይቅ ነዉ። መታረም አለበት። አባላትም በዚህ ከደንብ ውጪ በሆነ ጉዳይ ላይ መሳተፍ የለባቸውም። በአጠቃላይ ይህ ውስጠ ደንብ በማን ነው የፀደቀው? በጋዜጣው ላይ ከ2 ዓመት በፊት 11 አባላት ብቻ ነበሩ ተብሏል። ‘11’ዱ ብቻ ናቸው ያፀደቁት? 425-11=414 አዲስ አባላት በደንቡ (bylaw) ላይ ውይይት ማድረግና ማፅደቅ ሲገባቸው ይህ አልተፈጸመም፡፡ ታዲያ ምኑ ምርጫ ሆነ? በአመራር ላይ ያሉ ሰዎች የሚፈልጉትን ግለሰቦች ለማስቀመጥ የሚጠቀሙበት ከግልፅነትና ከዴሞክራሲያው አሠራር ውጭ የሆነ ተግባር

ነው። እንዴትስ ነው ሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ይህን የሚያደርገው? የአባላቱ ሥልጣን ምን ላይ ነው ያለው? የማኅበረሰቡ አባላትና በሚኒሶታ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተወላጆች በዚህ ጉዳይ ላይ በመወያየት፣ መደረግ በሚገባው ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥተን መሥራት ያስፈልገናል። በማኅበረሰቡ ድረገጽ ላይ የተቀመጠውን ውስጠ ደንብም ከድረገጹ ላይ ማየት ያስፈልጋል። ሜይ 16 ይደረጋል የተባለው ምርጫ በአግባቡ አስመራጭ ኮሚቴ ተመርጦ የተወዳደሪዎችን ስም ከጠቅላላ ተሰብሳቢዎች በግልጽ ተቀብሎ የማህበሩን አመራር አባላት እንዲያስመርጡ ጥረት ማድረግ የሁላችንም መብትና ግዴታ ነው። ከዚያም በውስጠ ደንቡ ላይ የሚደረገው ውይይት ይቀጥላል። ይህን ቀና አካሄድ አሁን በአመራር ላይ ያሉት ሰዎች መቀበል ይኖርባቸዋል፡፡

ሐ) በጋዜጣው ገጽ 6 ላይ አሁን በአመራር ላይ ያሉትን ሰዎች በሚመለከት እንዲህ ሰፍሯል፡- " ***በሌላ በኩል አሁን ያሉት አመራረ አባላት ይህን ኮምኒዩኒቲ ሲረከቡ 0 አካውንትና 11 አባላትን ብቻ በመሆኑ በጥቂት ጊዜያት አመርቂ ሥራ በመሥራታቸው ምርጫው አስፈላጊነት አይታየንም ሲሉ አስተያየት በመስጠት ላይ ናቸው"*** ተብሎ ተዘግቧል። እንዳዚህ ያለ አስተያየት ዝም ብሎ የሚታላፍ አይደለም። ዘ-ሐበሻ ግን ምንም ሳይል የእነሱን መልእክት አስተላልፎ የማህበሩን አባላትና በአጠቃላይ የሕዝባችን መብት ሲጣስ ዝም ከማለት የዚያን አስተያየት ሕጋዊነት ቢጠይቅ ኖሮ ጥሩ አካሄድ ነበር ። የአመራር አባላት ወቅታቸው አልፏል። አባላቱ ሲመርጧቸው ህብረተሰቡን ማገልገል እንጂ ራሳቸውን በራሳቸው ሥልጣን ላይ ማስቀመጥ አይችሉም። የአባላትን መብት መዳፈር ስለሆነ መቆም ያለበት ኢ-ዲሞክራሲያዊ አካሄድ ነዉ። ያለነው አሜሪካ ሕግና ደንብ የሚከበርበት አገር ውስጥ ነው። የኢትዮጵያ ማኅበረሰቡ (ኮምኒዩቲ) ማኅበራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ነው። የተወሰኑ ሰዎች የአባላትን የመምረጥ መብት ገፍፈው ራሳቸውን ወይም እነሱ የሚፈልጉትን ግለሰቦች በአመራር ላይ የሚያስቀምጡበት ሊሆን እንደማይችል እናስታውቃለን።

መ) በጋዜጣው ገጽ 6 እንደገና የአባላትና የሕብረተሰቡን መብት የሚጥስ አስተያየት አለ። "... ***የኮምዩኒቲ አባላት ቁጥር 11 ብቻ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የአባላት ቁጥር 425 መድረሱ እንደ ትልቅ ስኬት መቆጠር አለበት የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች አሁን ያለው አመራር የኮምኒቱኒቲውን ሕንፃም ሆነ ሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶች ስላሉ እነሱ እስኪፈጸሙ ድረስ አመራሩ ባለበት መቀጠል አለበት የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች"*** አሉ በማለት ጋዜጣው ጥያቄውን ለአቶ መስፍን ነጊያ ያቀርባል። ትላልቅ የተባሉት ፕሮጀክቶች አልተገለጹም፡፡ የሕንፃ ግዢውን በሚመለከት ጊዜያቸውን ሰውተው ከፍተኛውን ሥራ እየሠሩ ያሉት የሕንፃ ኮሚቴ አባላት ናቸው። እነሱ ሕንፃው እንዲገዛ ከሚፈልጉ በሚኒሶታ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወደ $50,000 እንዲዋጣ አድርገዋል። በተጨማሪም ለሚኒሶታ ኢትዮጵያውያን በግለሰብ አንድ ቲኬት $30 በመሸጥ ወደ $150,000 ለመሰብሰብ አቅደዋል። ለምን የእነሱ ውለታ አልተነሳም? "የበሬውን ውለታ ወሰደው ፈረሱ..."እንደተባለው መሆኑ ነው። ለአባላት ቁጥር መጨመርም ከፍተኛውን ሚና የተጫወተው የሕንፃ ግዢ ጉዳይ መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል። 30,000 ያህል ኢትዮጵይውያን ባሉበት ከተማ የማህበሩ አባላት ቁጥር 425 ደረሰ መባሉም የሚያስፈነድቅ ኣይደለም። ገና ብዙ ይቀረናል። በማኅበረዊ አገልግሎትም ድርጅታችን/ማኅበረሰቡ/ ገና በምኞት/ዕቅድ/ ደረጃ ላይ ብቻ ስለሆነ በሕዝብ ተሳትፎ መጎልበት አለበት። ያለው አመራር ጥሩ ሥራ ሠርተናል በማለቱ ኅብረተሰባቡ ተተኪ የአመራር አባላትን የመምረጥ መብቱ ሊገደብ አይችልም። ዘ-ሐበሻ በሚኒሶታ የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ አባላት መብት እንዲከበር አሁን አመራር ላይ ያለውን የሚደግፉ አስተያየቶችን ብቻ አቅርቦ ከማለፍ በገለልተኝነት እውነትን ፈልፍሎ እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል፡፡ አባላት አሁን ያሉትን አመራሮቹን ከፈለጓቸው ገምግመው መምረጥ ወይም አለመምረጥ መብታቸው ነው። ነገር ግን ከምርጫው ቀን በፊት በአመራር ላይ ያሉ ግለሰቦችን የምረጡልኝ ቅስቀሳ ዓላማ ቅንነት የጎደለው ስለመሆኑ ሕዝቡ እውቆ እንዲፈርድ እናስታውቃለን።

ሠ) በጋዜጣው ገጽ 6 ላይ " ***የኢትዮጵያ ኮምኒዩቲ መተዳደሪያ ደንብ በየ 2 ዓመቱ ምርጫ ይደረግ እንጂ በየ 2 ዓመቱ አመራሩ ይቀየር ኣይልም በመሆኑም ሕዝብ ቀጥሉ ቢላችሁ ትቀጥላላችሁ ወይ?*** በማለት ዘ-ሐበሻ አቶ መስፍን ነጊያን ይጠይቃል። አቶ መስፍን ነጊያም "**ሕዝቡ ቀጥሉ ካላም እንቀጥላለን ውረዱ ካላም እንቀጥላለን** "ካሉ በኋላ አሁን አመራር ላይ ያሉት ግለሰቦች በአመራር ላይ እንዲቀጥሉ ቅስቀሳ በማድረግ በሕዝብ ላይ ቀድመው የአስተሳሰብ ለውጥ ለመፍጠር ዘ ሐበሻን ተጠቅመውበታል። ይህ የዘመኑን ዲሞክራሲያዊ አሠራር የማይከተል ስለሆነ ተቀባይነት እንደሌለው እናስታውቃለን፡ ፡

ረ) በ4/05/2015 በተደመጠው KFAI ሬዲዮ የኢትዮጵያ ድምጽ ላይ ቀርበው ውይይት ሲያደርጉ ከሕንፃ ግዢ ኮሚቴ አባላት ለቀረቡት ጥያቄዎች ሦስቱም አሁን በአመራር ላይ የሚገኙት የቦርድ አባላት አስመራጭ ኮሚቴንና የምርጫ አካሄድን

በሚመለከት የስጡት መልስ የሚከተለው ነው፡- “**አስመራጭ ኮሚቴ የሚል በሕግ ደንቡ የለም፤ ያም አይደረግም**” በማለት ም/ሊቀመንበሩ ሲመልሱ ገንዘብ ያዡ ደግሞ “ **የቦርዱ ሊቀመንበር ነፃ (independent ) የሆኑ ሰዎችን መርጦ ምርጫው በሚካሄድበት ጊዜ እንዲቆጥሩና Certify አድርገው ለህዝቡ እንዲያሳውቁ ሕገ ደንቡ( Bylaw) ይጠይቃል። ያን ተከትለን እንፈጽማለን። በተረፈ ግን የመተዳደሪያ ደንቡ አስመራጭ ኮሚቴ እንዲናቋቁም አይጠቅም።** “ ብለዋል። እንዲሁም የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊውም “... **ግልጽ ለማድረግ የምንፈልገው አሁንም ቢሆን የኢትዮጵያ ኮምኒቲ በሚኒሶታ ቦርድ አባላት ተተኪ የቦርድ አባላትን የሚያስመርጡት በሕገ ደንቡ መሠረት ይሆናል።** ” ለአንድ ምርጫ አስፈላጊ የሆነውን አስመራጭ ኮሚቴን በቅድሚያ በሕዝብ መመረጥና የግልጽነት ጥያቄን ሦስቱም የአመራር አባላት ውድቅ አድርገዋል። ነፃ የምርጫ ተቆጣጣሪ የሚሉት ነፃ መሆናቸውን ማን ነው የሚወስነው ? ሊቀመንበሩ ብቻ? ይህ ማንንም አያሳምንም። አስመራጭ ኮሚቴ ከተሰብሳቢዎች በግልጽ ተጠቁሞ እንዲመረጥ፣ ተመራጮችንም እንዲያስመርጥ የማኅበረሰባችን አመራር በአግባቡ እንዲካሄድ ሐሳብ ሲያቀርብ ከነበረው የሕንፃ ግዢ ኮሚቴ አባላት ውስጥ ለምክትል ሊቀመንበሩ አንድ መሠረታዊ ጥያቄ አቀርቦ ነበር፤ ጥያቄውም “**በአንተ ትርጉም አስመራጭ ኮሚቴ ምንድነው? ለምን መመረጥ የሚፈልጉ ሰዎች እናንተ ቢሮ መደወልና ስማቸውን መስጠት አስፈለጋቸው? የቱ ቦታስ ነው ውስጠ ደንቡ ይህ መሆን አለበት የሚለው?** ላሉት ጥያቄ ም/ሊቀመንበሩ ምንም ተጨባጭ መልስ አልሰጡም። በመጨረሻ አንድ በልባቸው ያለውን እኛም የምንጠረጥረውን ሐሳብ እንዲህ በማለት ገልጸዋል። “ እንፎርምድ ( informed ) የሆነ ግለሰብ ምርጫ ውስጥ ቢገባ ጥሩ ነው የሚሆነው” ብለዋል።

ሕዝቡ እንዲረዳ የምንፈልገው ውስጠ-ደንቡ በግልጽ ለሕዝብ አለማሳወቃቸውና በማኅበረሰቡ ድረገጽ ላይ የተቀመጠውን ደንብ ማን እንዳፀደቀው አለመታውቅ የድብብቆሽ ጨዋታ ለማመቻቸት መሆኑን ነው። በአጠቃላይ ሐሳባቸው ሲታይ ራሳቸው አስመራጭ ራሳችው ጠቁዋሚ፣ ራሳቸው ተመራጭ ለመሆን እየተጣጣሩ ነው። አንድን ተመራጭ መገምገም የሚችሉት በጠቅላላ በሰብሰባ ወቅት አባላት ናቸው። የማኅበረሰቡ አባላት ሙብት ተውጦ ም/ሊቀመንበሩ ውስጥ ለውስጥ ለማተካካት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው እናስታውቃለን።

በሚኒሶታ የሚገኛው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ማኅበረሰቡን ለማጠናከር፣ የሥራ አመራሩን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድና በአባላቱ ሕዝብ የአስመራጭ ኮሚቴ ተመርጦ በአስመራጭ ኮሚቴው በኩል የተመራጮች ጥቆማ ተካሄዶ፣ አባላት ተመራጮችን መጠየቅ የሚገባቸው ጥያቄዎች ቀርበው፣ ምርጫው በግልጽ እንዲካሄድ ሙብታችንንና ግዴታችንን እንድንወጣ እናሳስባለን። አሁን ያለው አመራር የሰብሰባውን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በግልጽ እንዲያሳውቅ ማድረግ የሁላችን ሙብትና ግዴታ ነው። እንደ አቅማችን በዓመት ከ $30 እስከ $60 በመክፈልና የመክፈል አቅም የሌለው በነፃ የአባልነት ቅጽ ሞልቶ የማኅበረሰቡ አባል በመሆን አመራሩን በመምረጥ፤ ማኅበረሰቡን በሐሳብ፣ በጉልበትና በሁሉም መልኩ መርዳትና ማጠናከር ያስፈልጋል።

በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ድምፅ ራዲዮ ጣቢያ ገለልተኛ በሆነ መንገድ ሁሉንም ወገን ለማቅረብና የሚኒሶታ ሕዝብ ምርጫውን በሚመለከት አስተያየት እንዲሰጥ እያደረገ ያለው አስተዋፅዖ የሚደገፍ መሆኑን እንገልጻለን። ያሳየውን ሕዝባዊ አገልግሎት የምርጫው ሂደት በሕጋዊ መንገድ የሕዝብን ድምፅ ተከትሎ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ እንደሚቀጥል ተስፋ እናደርጋለን፡፡

**በሚኒሶታ ፍትሐዊ ምርጫ ፈላጊ ግብረ ኃይል**